EthioLion

የጐንቻው!

# “ ስፍሩን ለሰፋሪ ! ”

የሰፈሩ አለቃ ጐጠኛው ጠበብት፤
በእራስ ሕመማቸው ዘዎትር የሚያኩት፤
በዘር ቂጥኛቸው የመለጡ አናት፤
ቆስለው ያቆስሉናል ‘ቁልቋል ባላባት’፡
**አገር ይስፈራቸው በሰፈሩበት።**

ደቡብ ‘ጉራ ፋርዳ’ አማራ አፈናቅለው፤
በሺዎች ደም እንባ እጃቸውን ታጥበው፤
ያጉረጠርጣሉ ሌባ ጣት ቀስረው፤
‘መዓድ ዕድር’ ሰባሪ ያጐረሰ ነክሰው፤
ገርፈው ይጮሃሉ ሸንጐ ተፎጥጠው፤
**ባቀኑበት ቁና ስፍር ያማራቸው።**

እኒህ ዋልጌ ‘ዳኛ’ ዘር ጫሪ ቆፋሪ፤
‘ምርጥ ዘር’ አባዝተው ማሳ እርስት ወራሪ፤
ድንኩ አፈቀላጤ ትንሽ ፈታውራሪ፤
ጥፋተኛ ልማት አራጊ ፈጣሪ፤
‘አገር በቀል ንጉሥ’ ለደን ተቆርቋሪ፤
‘አማራ መጤ ነው’ ‘አክሳይ ነው መንጣሪ’፤
አርፎ የማይተኛ በእጅ እግሩ ቆፋሪ፤
ደቡብ ‘ሸንኮራ’ እንጂ አይሻም ታታሪ፤
‘የምስራቅ ጐጃም ሕዝብ’ ጉራፋርዳ ነዋሪ፤
‘አውዳሚ ነው’ አሉ ቋንቋው አስነዋሪ፤
ገዳዩ፤ቀማኛ መቶ ሺህ አባራሪ፤
**የት ነው? ትውልዳቸው የወያኔው መሪ።**

ሰፈራችን በዘር በእትብት ከተሰላ፤
ማነው? አራት ኪሎ ‘አረም’ የበቀላ፤
ማነው? ቤተ-መንግሥት የገባ በጅምላ፤
ማነው? ቤተ-እምነቱን፤መቅደሱን የሞላ፤
ባለመለዮቹስ?    ጄኔራል ጠቅላላ፤
**ስፍር  ለሰፋሪው  ጓዙን  ይጠቅላላ።**

አብራሪ አባራሪ የመሸጉበት፤
ፋኖ ፋንጢራዎች የኰነሱበት፤
በዞን ኦሮሚያ ‘ደደቢት ግዛት’፤
በዘር ከተቋጠርን ከገባን ስሌት፤
ማነው? አየር ኃይሉ በደብረ ዘትይት፤
**አገር  ይስፈራቸው  በሰፈሩበት።**

ደም ለውሰው አጥንት ሲሚንቶ ልባስ፤
በሙታን መቃብር ሞልተው ግብስባስ፤
እጅ እግሩን ተሳስሮ እንዳይላወስ፤
መሃል አገር ሕዝቡ ኑሮው ሲኰስስ፤
ተሳስረው፤ተዛዝለው ‘መረብ በመለስ’፤
ዘር መሰላላቸው እንዳይበጠስ፤
የቱጃሮች ሃውልት ‘ኢፈርት’ ሲነግስ፤
አዲስ ፎቅ ህንፃቸው የሰማይ ጠቀስ፤
የቁም ጣዖታቸው እምነት የሚያረክስ፤
ቦሌ ‘አዲስ ስግስጐች’ ማን ይባል ባምቢስ፤
‘ምሥራቅ ትግራይ’ ማዶ ‘አድዋ ቀመስ’፤
ዘር ፍትህ ከሆነ?  ‘መጤ ይመለስ’፤
ወያኔዎች ይውጡ ደደቢት ድረስ፤
**ባዶ እጅ፤ባዶ እግሩን የምሱን ይቅመስ።**

የጐንቻው!
yegonchaw@yahoo.co.uk

Ethiopia Will Prevail!
EthioLion.Com

# ማስታወሻ፡-

- የአረመኔውን ‘መለስ’ እና እንዳሻ የሚያዝዙትን ወራሪ ጉጅሎዎች መላ ኢትዮጵያዊ አሁንም እንደ ‘አገር መሪና’ እንደ ‘መንግሥት’ የሚያይ ሆደ ሰፊ ሕዝብና ፓርላማ በነዚህ ወገኖቻችን ላይ የደረሰውን፤የሚደርሰውን ግፍና በደል ለዓለም አሳፋሪ ስለሆነ ቢያንስ የይስሙላ እንኳ መፍትሔ ይሻሉ ተብለው በተማጽኖ ተጠብቀው ቢጠየቁ፤ ‘ርዕሰ ብሄር’፤ ‘መንበር’ ላይ ተቀምጠው የሰጡት ምላሽ፤ጭራሽ ንቀት፤ስድብ፤የተሞላበት እጅግ ትንሽነታቸውን በትልቁ አግዝፎ የሚያሳይ ምሳሌነታቸውን አረጋግጠዋል።

- እንኳንስ ሊጸጸቱ ቀርቶ እርሳቸው በሺዎች የሚገነድሏቸውን፤አባወራዎች፤ጅምላ የሚመነጥሯቸውን እንከን የለሽ የዋህ ትውልዶች፤ ለሰው ኃይዎት ከመጤፍ የማይቆጥሩ ወሮበሎች ደርሰው የአዛኝ ቅቤ አንጓች ሆኑና የጉራፋርዳን የተፍጥሮ ሃብት ተንከባካቢ፤የነዋሪውን ባህል ጠባቂ መሰሪ፤የምስራቅ ጐጃም ሕዝብ ደን መንጣሪዎች፤አውዳሚዎች፤አማራና አማርኛ ተናጋሪ ሁሉ ወንጀለኞች ናቸው ብለው ይፈርጃሉ፤ በትዕቢት ተወጣጥረው እንኳንም ተባረሩ፤ ‘ፕረዝደንት ሽጉጤ አበጀህ! የልቤን አድራሽ ነህ ነው ያሉት፡ አልፈውም እናንተን ምን አገባችሁ? እያሉ በንቀት አቀረሹብን።

- በአገራችን እርዕሰ መዲና፤ በየጐዳናው፤ሕጻናት፤አረጋዊያን ነፍሰጡርና የታመሙ፤የደከሙ፤ያለ እለት ልብስ፤ጉርስ መጠለያ ሲንከራተቱ ያስጠጓቸውን፤በአቅማቸው የደረሱላቸውን ወገኖች፤ድርጅቶች ሁሉ ነቅሰውና ወርፈው ‘በሽብርተኛ መተታቸው’ ደጋግመው እንደሚቆፈጿቸው ዝተዋል።

- እነዚህን ከስቃይና ከገሃነም ስደት ተርፈው የወገናችሁን እርዳታ ለምን ጠየቃችሁ ተብለው በቅልብ የኢጋዚ ጦርና በተናካሽ የብአዴን ስኳዶች የደከመ አካላቸው ከሚችለው በላይ እየተደበደቡ በጨለማ ተግዘው ተወስደዋል። የእኒህ ወገኖቻችን እጣ ፈንታ እስካሁን በትክክል አይታወቅም፤ አንዳንድ ዘገባዎች እንደሚያመለክቱት፤ከሆነ በግፍ ተግዘው ጅምላ እስር ቤት፤በረሃ፤ደን፤ዋሻ እና ባዶ መጋዘን ታጉረው በረሃብ፤በጥማት፤በህመም፤በድብደባ እንዲሞቱ እየተደረገ ነው፡ በአካልም ሆነ በስልክ የሚያደርጉት ግንኙነት ሙሉ በሙሉ ተቋርጦ በአሁን ጊዜ የጀርመኑ ናዚ ሂትለር በጂውሾች ላይ እንደፈጸመው ዓይነት የዘር ማጥፋት ወንጀል ሊካሄድባቸው እንዲሚችል ከባድ ስጋት አለ። ይህ አናሳ ጉጅሌ ይኸንን ከማድረግ የማይመለስ የዘቀጠ የጥፋት ብርጌድነቱን በአገራችን ልዩ፤ልዩ ቦታዎችና ጊዜያት አስመስክሯል።

- ለማፈናቀል በእቅድ የተያዙት ወደ ሰማኒያ ሺህ የሚጠጉ ወገኖቻችን ላይ ያንዣበበው የጥፋት አደጋ ከብዷል፤ ሌት በጨለማ ቀን በጠራራ ጸሃይ ሰው እንዳይ እንዳይሰማ ተደርጎ ወከባው ተጧጡፎባቸዋል። በየጊዜው አፈትልኮ የሚወጣው ዜና እጅግ ዘግናኝ ነው።

- ይሁንና ‘መለስና ጉጅሌዎቹ’ በኢትዮጵያ ሕዝብና ወገን ‘ጠባብ መንጋቸውን’ አስታጥቀው ስልጣን ሃብት ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥረው ሲደላደሉ፡ ሌላው በአገሩ ሁለተኛና ሦስተኛ ዜጋ ሆኗል። ቤተ መንግሥት፤ቤተ እምነቶችን የአገርና የሕዝብ ተቋማትን የንግድና የተለያዩ የስራ መስኮችን ሁሉ ተሻምተው፤የአገር መከላከያው፤የደህንነቱ፤ሁሉ በጐጠኝነት በተለይ ‘በትውልድ ትግራይና በአድዋ መንደርተኝነት’ በዘር በዝምድና በበላይነት ተቆጣጥረው ለ20 ዓመታት አንዳንዴም ከጣሊያን የውጭ ወራሪ ጠላት በከፋ ሲገድሉት፤ሲያዋክቡት፤ሲያዋርዱት የዜግነትና የትውልድ እትብቱን ሳይቆርጥ፤ የአያት ቅድመ አያቱን ቃለ መሃላ ሳያፈርስ፤ከነሱ በልጦና አስተውሎ በማሰብ፤ እንደ ህመምተኛ አካሉ፤እንደ ወገኑ ሲያስታምማቸው፤መጨረሻ በሌለው ትዕግሥት እናንተም ወደመታችሁበት ተመለሱ ሳይል፤ ሲማጸናቸው ኖራል።

- አሁን የጥፋታቸው አዙሪት አናታቸው ላይ ወጥቶ ከስካር ያለፈ እብደት ደረጃ ላይ አድርሷቸዋል፡ ስለሆነም በሕግም፤በሞራልም፤በእምነትም የማይዳኙ የለየለት የጥፋት አረመኔያዊ ግፍ እየደገሱ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሚሊየኖች የሚያጫርሱበትን መሰሪ አደጋ እየቆፈሩ ይገኛሉ። ከነዚህም አንዱ እስላምና ክርስቲያኑን ለማናከስ፤ደቡብና ሰሜኑን ለማጣረስ፤የጥፍት ክብሪት በየገዳማቱና በየቤተ እምነቱ ለኩሰው የሚቀርብላቸውን የሕዝብ ጥያቄ አንቋሸው አርክሰው ይዝታሉ፤ይህም ወደ እማያባራ የእልቂትና የነውጥ ቀውስ እንዲያመራ የሚቋምጡት መለስና ጉጅሌዎቻቸው ብቻ ናቸው።

- የኢትዮጵያ ሕዝብና ወገን ሆይ ይኸንን የጥፋት ማዕበል ለመታደግ በአንድ ላይ እንቁም። ለምድሩም፤ለሰማዩም ገኸ፤አስተዳዳሪና መሪ ሁሉ አቤቱታ እናቅርብ፤ያለመሰልቸት፤በየቀኑ፤በየሰዓቱ ይህንን እኩይ አደጋ እናጋልጥ፤ በጋራና በግል ደግሞ እንደ አቅማችን እንታገላቸው ለእነዚ ወገኖቻችን በዚህ የስቃይና የጨለማ፤የጭንቅ ሰዓት እንድረስላቸው፤አገር፤ትውልድ፤ዜጋ፤ታሪክ አውዳሚዎችን፤ እንድንፋረድ፤በቃ! በቃ! በቃ! ብለን እንነሳ።

- ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ ፈጣሪያዋ ዘርግታለች። ኃይልም የፈጣሪ ነው።

EthioLion.Com